# መመሪያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** ABA, ABC, ABC-RA, ACA, ACD, ACG, ACG-RA, ACG-RB, DNA, ECM, ECM-RA, FAA-RA, JEE, JEE-RA

**ሃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** ዋና የሥራ ኃላፊ

## የትምህርት መገልገያዎች እቅድ

A. **ዓላማ**

መማር፣ ግንኙነቶች፣ መከባበር፣ ምጡቅነት፣ እና ፍትኃዊነት የመሣሠሉትን የቦርዱን ዋና ዋና እሴቶች ጋር የሚጣጣም እያንዳንዱን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ለስኬታማነት በደንብ ለመዘጋጀት የሚያስችል ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ፋሲሊቲዎችን የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድን ጥረት ለማረጋገጥ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የትምህርት ፋሲሊቲዎችን ፍላጎት በትክክል ያገናዘበ የማቀድ ሂደት ለማቋቋም እና ፍትሃዊነት ያለው እና ባልተረጋገጠ የወደፊት ሁኔታ ላይ ቅድሚያ መስጠት ያለባቸውን የማስተማር ፕሮግራሞችን ታሳቢ የማድረግ የት/ቤቶችን ህንጻዎችን ይዘቶች፣ በዝቅተኛ ወይም ከመጠን በላይ ፋሲሊቲዎችን የመጠቀም ሁኔታ በትምህርታዊ ፕሮግራም ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ሃላፊነት የተሞላበት የፋሲሊቲ ውሳኔ ማእቀፍ እቅድ ለመመስረት

ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ፋሲሊቲዎች የማቀደ ሂደት እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ማሳወቅ/ማወቅን ማዳበር፣ እና ለእነዚያ ኩነቶች ምላሽ መስጠት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፋሲሊቲዎችን በእቅድ የመስራት ሂደት ከሌሎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ከሚገኙ የአካባቢ የመንግስት እና የማዘጋጃ ቤቶች ተቋማት ጋር ለማስተባበር

B. **የቀድሞ መነሻ**

ለሁሉም ተማሪ ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ታህታይ መዋቅር/መሠረተ ልማት ለይቶ ለማወቅ የትምህርታዊ ፋሲሊቲዎች (መሳሪያ፣ ህንጻ፣ አገልግሎት ወዘተ) እቅድ/ፕላን አስፈላጊ ነው። በተማሪዎች ምዝገባ ላይ ለሚከሰቱ ለውጦች፣ ትምህርታዊ ፕሮግራም፣ እና የህንፃ ሥራ መሠረተ ልማት ምላሽ በመስጠት የ MCPS ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ከፍተኛ ጥራት እንዲኖረው ስለ ትምህርታዊ ፋሲሊቲዎች (መሳሪያ፣ ህንጻ፣ አገልግሎት ወዘተ) እቅድ/ፕላን ማዘጋጀት የትምህርት ቦርድ መሠረታዊ ኃላፊነት አለበት።

C. **ጉዳይ**

1. በርካታ ተማሪዎችን በመቀበል ረገድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በአገሪቱ ከፍተኛ ከሚባሉት አንዱ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በግምት 500 ስኩዌር ማይሎችን የሚያካትት እና ከገጠር እስከ ከተማ የተለያየ የማህበራዊ ስብጥር ክምችት ያለበትን ካውንቲ ያገለግላል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ያለበት ሁኔታ የንግድ እና የመኖሪያ ማእከሎች፣ እንዲሁም ባለፉት ጥቂት አስርተ አመታት እያደገ የመጣው የትራንስፖርቴሽን መሠረተ ልማት የተማሪ ቁጥር መጨመር ላይ ተጽእኖ አለው።

2. የትምህርት ቤት ፋሲሊቲዎች የትምህርት ፕሮግራሞችን ፍላጎት የማሟላት ችሎታ በጊዜ ሂደት ይቀየራል። ለትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ተገቢ የሆኑ ቦታዎችን መስጠት/ማመቻቸት፣ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች ሠላማዊ፣ ስጋት የሌለበት፣ ጤነኛ የትምህርት የሥራ አካባቢዎችን መስጠት እና እያረጁ የሚገኙ ህንፃዎችን እና የህንፃ መዋቅሮችን ተመጣጣኝ በሆነ ወጪ ተስተካክለው እንዲጠበቁ ማድረግ ቦርዱ በተከታታይ የሚያጋጥመው ተግዳሮት ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁሉንም ት/ቤቶች ያለው ንብረት ፋሲሊቲዎችን በተባበረ የጊዜ ሠሌዳ ጥገና እና እድሳት በማድረግ፣ በመተካት በቀጣይነት ረዘም-ያለ እድሜ ከፍተኛ ደረጃ አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት ደረጃ እንዲጠበቁ ከናድረግ ጥረት ያደርጋል። ከጊዜ ወደ ጊዜ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ እና የግንባታ ኮዶች በስፋት እየተሻሻለ/እያደገ መሄድ በተለያየ ጊዜ የተገነቡ ወይም የተገጣጠሙ ህንፃዎችን መዋቅር እድሜ ከማራዘሙም በላይ ቦርዱ የትምህርት ፋሲሊቲዎችን ፕላን የማድረግ ሂደት የሚያስፈልገው ከሆነ ጊዜ በኋላ ለትምህርት ፋሲሊቲዎቹ ወይም ተዳኝ ለሆኑ መገልገያ ህንጻዎች እድሳት/ጥገና ጠቃሚ እንደማይሆን፣ እና ሲስተሙን መቀየር ወይም ከወቅቱ የትምህርት ፕሮግራም ጋር ለማጣጣም ከፍ ያለ የካፒታል ፕሮጀክት ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን ነው።

3. የትምህርት ፋሲሊቲዎች ፕላን የማድረግ መሠረታዊ ግብ እየጨመረ በመጣው የተማሪዎች ቁጥር፣ ተማሪዎችን በጂኦግራፊያዊ የት/ቤቶቹች ስብጥር ለመመደብ፣ እና የዘረኝነት፣ የጎሳ፣ እና በትምህርት ፕሮግራም ላይ ሌሎች ማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ እና የብዝሃነትን ስብጥርን ትርጉም ያለው የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ነው። የተማሪ ቁጥር መጨመር በተለያዩ በርካታ ምክንያቶች የሚከሰት ሲሆን ይኼውም፡- የኢኮኖሚ እና ስራ የማግኘት ቁጥር እድገት፣ የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ መስተዳድር ፖሊሲ ድንጋጌዎች፣ በመኖሪያ ቤቶች እድገት የሚከሰት የገበያ ለውጥ እና በመሬት አጠቃቀም ረገድ ሌሎች ለውጦች፣ በቤተሰብ ስብጥር የሚከሰቱ ለውጦች፣ የመውለድ መጠን መለዋወጥ፣ የት/ቤቶች ክልል መለዋወጥ፣ በትምህርት ሲስተሙ እና ወደ ትምህርት ሲስተሙ ከሌሎች የዩናይትድ ስቴትስ አካባቢዎች እና የዓለም ክፍሎች በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ምክንያት ይቀያየራል።

## D. አቋም

ቦርዱ የሚከተሉትን አካላት የሚያካትቱ የትምህርት ፋሲሊቲዎችን ፕላን የማድረግ ሂደት ይፈልጋል፡- ቀጣይነት ያለው የተማሪ ምዝገባ ዝርዝር ሁኔታዎችን ታሳቢ ማድረግ፣ የትምህርት ፋሲሊቲዎች እና ህንጻዎች ሲስተም ያሉበት ሁኔታ፣ ስለ ፋሲሊቲው ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ፣ ፈጣን የሆነ አማራጭ ምላሽ የሚሰጥ እና ተመጣጣኝ፣ በሁሉም የአካባቢ፣ ስቴት፣ እና የፌደራል መስፈርቶችን የሚያሟላ ኃላፊነት የተሞላበት የገንዘብ/ባጀት አጠቃቀም እና ትርጉም ያለው የትምህርት ውሳኔዎች ማእቀፍ ያካትታል።

ይህ ፖሊሲ የትምህርት ፋሲሊቲዎች ፕላን ሂደት ስኬታማ እና ኃላፊነት የተሞላበት የገንዘብ አጠቃቀም መንገድ የተለያየ አይነት የትምህርት ፍላጎት ላላቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ቀጣይነት ያለው የትምህርት አካባቢን ለማመቻቸት መመሪያ ይሰጣል። አሠራሩ የተነደፈው ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ ሂደት የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ እና ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ የማህበረሰብ አባላት እና ድርጅቶች፣ የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር ኤጀንሲዎች፣ እና ማዘጋጃ ቤቶች አስተዋጽኦ የማድረግ እድሎች እንዳሏቸው ለማረጋገጥ ነው።

1. ስራ የሚያቀላጥፍ (መሳሪያ፣ ህንጻ፣ አገልግሎት ወዘተ) እቅድ የሚጀምረው በተማሪ ምዝገባ የሚወሰድ ግምት/ፕሮጀክሽን ትንታኔ/ዝርዝር ጥናት/analysis፣ ለትምህርት ፕሮግራም የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ የፋሲሊቲ አጠቃቀም ሁኔታ፣ ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ቦታ ስፋት፣ የመያዝ አቅም ስሌት፣ የካውንቲው እቅድ እና የእድገት አቅጣጫ፣ የመሬት አጠቃቀም፣ መጓጓዣ፣ እና የመኖሪያ ቤት አኳኋን፣ እና ከዚህ በታች D.1.c ላይ የተዘረዘሩት ቁልፍ የስራ ማቀላጠፊያዎች።

   a) አስፈላጊነቱ ግምት የተሰጠው የትምህርት ፕሮግራም በስራ ላይ ያለውን እና አዳዲስ

ፕሮግራሞችን አቅርቦቶች፣ ስለተማሪ ምዝገባ የሚወሰዱ ግምቶች/projections እሳቤ መወሰድ ያለባቸው የስነ-ህዝብ ስብጥር መለዋወጥ።

b) የትምህርት ቤት ስፋት እና መጠን ስሌት ቦርድ ካጸደቀው የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንዳንት ስለ ካፒታል የማሻሻያ ፕሮግራም ክፍል/አካል ያቀረቡት መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማገናዘብ።

c) ቁልፍ የሆኑ የስራ መገልገያዎች/ፋሲሊቲዎች (መሳሪያ፣ ህንጻ፣ አገልግሎት ወዘተ) የትምህርት እና የሥራ ሁኔታ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ የአካባቢ ሠላም፣ ደህንነት፣ እና ለደራሽነት ተፈላጊ ነገሮች፣ የአካባቢ ውስጣዊ ሁኔታዎች፣ የፕሮግራም እና የቦታ አመቺ ግንኙነት ሁኔታ፣ የህንጻው ጥራት፣ እንዲሁም ሌሎች የመሠረተ ልማት እና ንብረት መረጃ፣ እና ሌላ ጠቃሚ መገለጫዎች።

d) ቁልፍ የሆኑ የስራ መገልገያዎች/ፋሲሊቲዎች (መሳሪያ፣ ህንጻ፣ አገልግሎት ወዘተ) አመላካች አቀራረብ የሚሠራበት እየተቀየረ/እየተለወጠ ላለው የፋሲሊቲ ፍላጎት ቅደም ተከተል አማራጮችን ለመለየት ነው። በካውንቲ አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ሲስተም የመተካት ፕሮጀክቶች እና የአንዳንድ ት/ቤቶች ትላልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶች ተቀባይነት ኖሯቸው የቦርድ የሚመለከታቸት የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንዳንት የታቀዱ የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም በማድረግ ከዚህ በላይ በተገለጸው ትንታኔ አኳኋን ክለሳ ይደረግባቸዋል። እነዚህ አማራጮች የሚያካትቱት-

(1) ትምህርት ቤቶችን በተፈላጊው ጥሩ ሁኔታ ለማቆየት ጠቃሚ የሆኑ እና የጠቃሜታነታቸውን እድሜ ለማራዘም ለምሳሌ:- የሙቀት፣ የአየር ዝውውር ማስተካከያ፣ የአየር ሁኔታ ማስተካከል፣ እና መካኒካል ሲስተሞችን፣ ጣራዎችን፣ እና በርካታ ሌሎች የህንጻ እና መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ካውንቲ-አቀፍ ሲስተም የመተካት ፕሮጀክቶች፣ እና

(2) መጠኑን ለማሳደግ፣ እድሳት፣ ማስተካከያ፣ ለሌላ ዓላማ ማዘጋጀት፣ ወይም በአገልግሎት ላይ ያሉትን ፋሲሊቲዎች ለመተካት፣ ወይም ያሉትን እንደገና ለመጠቀም ወይም ያለውን ቦታ አሻሽሎ በሌላ ፋሲሊቲ እንደአስፈላጊነቱ የመጠቀም የተለየ ፋሲሊቲን የሚመለከቱ ዋና የካፒታል ፕሮጀክቶች።

e) የፋሲሊቲን ፕላን ማድረግ በተጨማሪም አቅምን ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑትን የፋሲሊት ፍላጎቶችን የካፒታል ያልሆኑ ስልቶችን/ስትራተጂዎችን ዝርዝር ጥናት ያካትታል።

(1) በርካታ ተማሪዎችን የመቀበል አቅማቸው አነስተኛ የሆኑ ትምህርት ቤቶችን መጠናቸውን ለማሳደግ እና/ወይም በዚህ ሳይወሰን፣ ነገር ግን ከመጠን በላይ አቅም ካላቸው ትምህርት ቤቶች መዛወርን ለማበረታታት፣ ካፒታልን የማይጨምሩ ስልቶች/ስትራቴጂዎች፣

(a) የወሰን/የድንበር ለውጦች፣ ወይም

(b) ለጂኦግራፊ ተማሪ ምርጫ የተመደቡ እቅዶች (እንደ ኮንሶርሽያ)፣ እና/ወይም

(2) የመቀበል ደረጃ ሲቀንስ ት/ቤት መዝጋት እና/ወይም ማጣመር።

2. እንዲህ ዓይነቱ ዝርዝር ጥናት የሚያመለክተው፣ ቦርዱ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል እና ከሜሪላንድ ስቴት ለካውንቲ አቀፍ ሲስተም የመተካት ፕሮጀክቶች እና ለከፍተኛ/ዋና የካፒታል ፕሮጀክቶች

ስለሚጠይቃቸው የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም ለማወቅ ይረዳል።

a) የስድስት ዓመት የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ነገሮች/ኤለመንቶች ያካትታል፡-

(1) የሚቀበለውን የተማሪ ብዛት መጠን ትልም/ፕሮጀክሽን፣ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች፣ በካውንቲ አቀፍ የሚገኙ የትምህርት ቤት አቅም እና የአጠቃቀም ደረጃዎችን

(2) section D.1.e)(1) ላይ እንደተደነገገው ካውንቲ አቀፍ ታሳቢ የተደረጉ ተተኪ ፕሮጀክቶች

(3) section D.1.e)(2) ላይ እንደተደነገገው ታሳቢ የተደረጉ አዳዲስ ፋሲሊቲዎች እና ትላልቅ ካፒታል ፕሮጀክቶች

b) በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት አማካይነት በየአመቱ ጁን ላይ የሚዘጋጀው የትምህርት ፋሲሊቲዎች/መገልገያዎች ማስተር ፕላን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል ስለ ካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም የተሰጡ ውሳኔዎችን በሙሉ በማጠቃለል ያመላክታል።

3. የረዥም ጊዜ እቅድ፡- ቦርዱ የረዥም ጊዜ ..ይጠቀማል (ማለት፡- ከስድስት ዓመት የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም ተሻጋሪ የሆነ) የእቅድ ሁኔታን ማእቀፍ የካፒታል ማሻሻያዎችን ፕሮግራም እድገት ለማስገንዘብ እና MCPS ለማደስ እና ከቴዳኅጂያዊ እና የትምህርት ፕሮግራም ጋር ለማጣጣም፣ ምን ያክል ተማሪ ለመቀበል እንደሚያስችል ያለውን ግመታዎች፣ የፋሲሊቲ አጠቃቀም መጠንን፣ የት/ቤቶችን አካላዊ ሁኔታ፣ እና ት/ቤቶች ያላቸውን አቅም እና መደበኛ ያልሆኑ ቦታዎችን ያሉትን የፋሲሊቲ አማራጮችን ለይቶ ለማወቅ ይጠቀማል።

4. የፋሲሊቲ እና የአቅም ፍላጎቶችን የመገንባት አጠቃላይ የዲስትሪክት ፈቃድ መሠረት፣ ትላልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶችን ለመሸከም የሚችሉ ፋሲሊቲዎች በጊዜያዊነት ይመደባሉ።

**E. የባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ**

1. ስለ አዳዲስ ትምህርት ቤቶች፣ የት/ቤቶችን ክልሎች ስለመለወጥ፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ አመዳደብ ምርጫ እቅዶችን መዘርጋት፣ ት/ቤቶችን ስለመዝጋት ወይም ስለማጣመር፣ እና ሌሎችም እነዚህን የመሣሠሉ ከፋሲሊቲ ጋር የሚገናኙ በት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንዳንቱ ተለይተው የሚቀርቡ ጉዳዮችን አማራጭ እርምጃዎችን እንዲያዘጋጁ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት ለሠራተኞች መመሪያ ይሰጣል።

2. በሠራተኞች ተዘጋጅተው ማህበረሰቡ ሃሳብ በመስጠት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የሚቀርቡት አማራጮች ከዚህ በታችን section G የተገለጹትን እያንዳንዱን እውነታዎች ለማስኬድ የተለያዩ አማራጮችን እና የቀረቡትን አማራጮች ለማስኬድ የሚችሉበትን ምክንያቶቻቸውን ጭምር መግለጽ አለባቸው።

3. Board Policy ABA ፖሊሲ መሠረት፣Community Involvement/የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ከዚህ እንደሚከተለው ሠራተኞች ባዘጋጇጇቸው አማራጮች ላይ የማህበረሰብ ተሳትፎ ስለሚኖረው ተጽእኖ ለሱፐርኢንተንዳንቱ ምክር ለመስጠት ዓላማ አስተዋጽኦ እንደሚያስፈልግ ለሠራተኞች መመሪያ ይሰጣል፡-

a) ከበርካታ ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ ለማግኘት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ሰፊ ውክልና እና ተሳትፎ እንዲኖር ለማትጋት ሱፐርኢንተንዳንቱ ለሠራተኞች መመሪያ ይሰጣል

b) እንደ ፕሮጀክቱ ሁኔታ፣ ስፋት እና መጠን፣ በሰፊው ለማሰባሰብ በርካታ ስልቶችን/ስትራተጂዎችን

በመጠቀም ከማህበረሰብ አስተዋጽኦ ለማግኘት ሱፐርኢንተንዳንቱ ለሰራተኞች መመሪያ ይሰጣል። ይህ ማህበረሰብን የመድረስ ስልት/ስትራተጂ የሚያካትተው፣ በዚህ አይጠቃለልም፣ በሲስተሙ የታቀፉ ኮሚቴዎችን፣ የትኩረት ቡድኖችን፣ የስራ ግረኃይሎችን፣ የስራ ቡድኖችን፣ በጠረጴዛ ዙርያ የውይይት ቡድኖችን፣ የዳሰሳ ጥናቶችን፣ በቴክኖሎጂ የሚታገዙ ግንኙነቶችን፣ እና/ወይም ሌሎች ለመተባበር የሚፈልጉ ፈቃደኝነት/ፍላጎት ያላቸው የሚመለከታቸው ክፍሎችን እና ለሠራተኞ ኢንፎርሜሽን/መረጃዎችን እና ግብረመልስ የሚሰጡ ሌሎች የእቅድ ሁነቶችን ያካትታል።

4. ከባለድርሻ አካላት ግብረመልሶች ከተሰበሰቡ በኋላ፣ የት/ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ ከባለድርሻ አካላት የትኩረት ግብአቶች ጋር ለቦርድ መቅረብ ያለባቸውን የማጠቃለያ ሃሳቦችን/አስተያየቶችን በማቀናበር ያዘጋጃል። ከትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ የተቀናበሩ አስተያየቶች ለህብረተሰብ፣ ለሚመለከታቸው የት/ቤት ማህበረሰብ፣ እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት እንደአስፈላጊነቱ ይቀርባል።

### F. የትምህርት ቦርድ በጥልቀት የሚካሄድ ውይይት እና የማህበረሰብ ሃሳብን መግለጽ

1. ከባለድርሻ አካላት የተገኙ ግብአቶችን በዝርዝር መገምገም ሂደት ተመርኩዞ ቦርዱ በአብላጫ ድምፅ፣ ከሱፐርኢንተንዳንት ሃሳቦች አንድ ወይም ይበልጥ አማራጮችን መለየት ይችላል። ከዚህ በታች section G ላይ የተጠቀሱት አንድ ወይም የበለጡ ምክንያቶች ከቦርድ የተሰጡ አማራጮች ተግባራዊ ደረጋሉ። የቀረቡትን ተለዋቾች ሠራተኞች በአማራጭነት ያዳብራሉ።

2. ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልል-ወሰኖች፣ የተማሪ ምርጫ ጂአግራፊያዊ ምደባ እቅድ፣ ወይም የትምህርት ቤት መዝጋት ወይም ማጣመር በተመለከተ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት የሚቀርቡ አስተያየቶች እና ቦርዱ እንደአማራጭ በሚያተኩርባቸው ላይ ቦርዱ ከህዝብ የሚቀርቡ አስተያየቶችን እና የጽሑፍ ምስክርነቶችን ያዳምጣል።

3. ቦርዱ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት የሚያቀርበውን ሃሳቦች/አስተያየቶች ወይም የተወሰኑ አማራጮችን ስለ ቦታ አመራረጥ፣ ስለ ት/ቤት ድንበር፣ ጂአግራፊያዊ የተማሪ የምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ወይም የማህበረሰብ አስተያየትን ተከትሎ የት/ቤት መዝጋት ወይም ማጣመር የቀረበው በቂ ተጽእኖ አይኖረውም ተብሎ በአብላጫ ድምፅ ከታመነ መጠነኛ ማስተካከያዎችን ለማድረግ ይችላል።

4. ቦርዱ ተግባራዊ የሆነ የስቴት ወይም የካውንቲ መስፈርቶች መሠረት ስለ ካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም እና ከላይ የተጠቀሱ የፋሲሊቲ እቅድ እንቅስቃሴዎች፣ በነዚህ ባያበቃም፣ ለአዳዲስ ትምህርት ቤቶች ቦታን መምረጥ፣ የት/ቤት ወሰን-ክልሎችን መቀየር፣ ለተማሪ ምርጫ የሚስማማ ጂአግራፊያዊ ምደባ እቅዶችን መመስረት፣ እና ያልተለመዱ/መደበኛ ያልሆኑ ክስተቶች ሲፈጠሩ ለመዝጋት ወይም ለማጣመር ቦርዱ ለመወሰን እንዲያመች በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት የተዘጋጀ የተለየ እና/ወይም በአንድነት የሚካሄድ ሂደት እና የጊዜ ሠሌዳን ሊያጸድቅ ይችላል።

### G. ትኩረት መሰጠት ያለባቸው ምክንያቶች

1. ለቦርድ የሚቀርቡ አስተያየቶች በሚዘጋጁበት ወቅት፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት ከዚህ በታች የተገለጹትን ምክንያቶች ወደፊት ለማስኬድ የሚያስችሉ ምክንያቶች ይቀርባሉ። እያንዳንዱ ምክንያት ታሳቢ ሆኖ ሳለ፣ እያንዳንዱን አስተያየት ማስታረቅ/ማጣጣም አመቺ ላይሆን ይችላል።

2. ለአዳዲስ ት/ቤቶች ቦታ ለመምረጥ፣ የት/ቤት ክልሎችን ለመለወጥ፣ ወይም በተማሪ ምርጫ የጂአግራፊያዊ ምደባዎች እቅድ ግምት መሰጠት ያለባቸው እውነታዎች

   a) የተማሪ ማህበረሰብ ስብጥር ባህርያት

አማራጮቹ በአጠቃላይ የሚነካቸው ት/ቤቶች ማህበረሰቦች ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ በአማራጮች ትንታኔ ወቅት መታየት ይኖርበታል። ከእያንዳንዱ የሚመለከተው ትምህርት ቤት የ Board Policy ACD መሠረት የተለያየ የተማሪዎችን ብዝሃነት የመፍጠር አማራጮች ላይ መተኮር አለበት። በጥራት ላይ ያተኮረ ትምህርት/Quality Integrated Education። የተለያዩ አማራጮች የሚያስከትሉትን ተጽእኖዎች የሚያመለክት የስነ-ህዝብ መረጃ/Demographic data የሚከተሉትን ያካትታል፦ የተማሪውን ህብረተሰብ የዘር/የጎሣ ስብጥር፣ የተማሪዎን ህብረተሰብ ማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ ስብጥር፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ደረጃ፣ እና በሌሎች አሳማኝ የሆኑ የልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ተሳትፎ ዎች የስነህዝብ አመላካች ሁነቶች።

b) ጂኦግራፊ

ህብረተሰቡ በትምህርት ቤቶች ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ MCPS ባለው ትኩረት መሠረት፣ አማራጮች መሆን ያለባቸው፣ የግዴታ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፣ ማህበረሰቡ ለትምህርት ቤት ያለውን ጂኦግራፊያዊ ቀረቤታ ግምት መስጠት፣ እና አወቃቀር፣ የትራፊክ ሁኔታ፣ እና የትራንስፖርቴሽን ሁኔታ እና መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ትኩረት መሰጠት አለባቸው። በተጨማሪ፣ አማራጮቹ ትኩረት መስጠት ያለባቸው፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክለስተር ውስጥ ያሉትን ትምህርት ቤቶች ብቻ ሳይሆን ቢያንስ በአዋሳኝ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ጭምር ነው።

c) በጊዜ ሂደት የትምህርት ቤት ምደባዎች መርጋት/ቋሚነት

አማራጮቹ በተቻለ መጠን ለረዥም ጊዜ የሚጸኑ ምደባዎች መሆን አለባቸው። እነዚያኑ ተመሣሣይ ተማሪዎች የሚመለከት ተማሪዎችን እንደገና ምደባ ሲደረግ በቅርብ የተደረገ የወሰን-ድንበር ወይም ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅድ ለውጦችን፣ እና/ወይም የትምህርት ቤት መዝጋት እና መጣመር ትኩረት መሰጠት አለበት።

d) የፋሲሊቲ አጠቃቀም

የትምህርት ቤት ክልል-ወሰን እና ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች በፋሲሊቲ አጠቃቀሞ በተቻለ መጠን በረዥም ጊዜ ከ 80 ፐርሰንት እስከ 100 ፐርሰንት ውጤታማ በሚሆን ደረጃ ላይ መተኮር አለበት። በማህበረሰቡ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት ፋሲሊቲን ከአንድ ክላስተር በላይ በጋራ የመጠቀም ፕላን በአንዳንድ ሁኔታዎች በጣም ውጤታማ ፕላን ሊሆን ይችላል። በተቻለ መጠን ፕላኖቹ የገንዘብ ወጪን ለመቆጠብ የካፒታል እና የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን የመቀነስ ኃላፊነት ሊኖራቸው ይገባል።

3. የቦታ ምርጫ

በቅድሚያ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ፣ አዲስ ትምህርት ቤት ስለሚከፈትበት ቦታ ግምገማ በሚደረግበት ወቅት፣ መደበኛ ያልሆኑ ቦታዎችን እና ለትምህርት ቤት ተብለው የተሰጡትን ወይም የተገዙትን እና በቦርድ ኢንቬንቶሪ የተመዘገቡትን ጨምሮ፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፦ አሁን ያለውን እና የወደፊት ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ክምችት እና ያሉት ት/ቤቶች፣ የኤከሬጅ ስፋት መጠን፣ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና ሌሎች ከባቢያዊ ሁኔታዎች፣ ዩቲሊቲዎች መኖራቸውን፣ ተፈጥሮአዊ/ፊዚካል ሁኔታ፣ በተፈለገ ጊዜ ለማግኘት እንደሚቻል፣ እና የግል ንብረት ከሆነ ለማግኘት የሚያስከፍለው ዋጋ/ወጪ።

4. የፋሲሊቲ ንድፍ/ዲዛይን

የትምህርት ፋሲሊቲ ንድፎች/ዲዛይኖች የማህበረሰብ አስተዋጽኦ ግብአት ግምት ውስጥ ማስገባት እና ጤናማ፣ ከአካባቢ ደህንነት ጥበቃ መርህ ጋር የተቀናጀ እና ከወቅቱ የትምህርት ፕሮግራም ፍላጎት ጋር እና ከወደፊት ፕሮግራም ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ መሆን አለባቸው።

5. ትምህርት ቤቶችን የመዝጋት እና የማጣመር ሂደት የሜሪላንድ ህግን እና የዚህን ፖሊሲ መመሪያዎችን የሚያሟላ መሆን አለበት።

## H. ተፈላጊ ውጤቶች

1. የትምህርት መገልገያዎች/ፋሲሊቲዎች እቅድ ሂደት ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ፋሲሊቲዎችን ይሰጣል።

    a) መሠረተልማቶችን እና ሌሎች ያሉትን አስፈላጊ አማራጮችን በመለየት፣

    b) ለወቅታዊ እና ይሆናሉ ተብለው ለተገመቱ ሁኔታዎች ምላሽ መስጠት፣

    c) ከወላጆች/ሞግዚቶች፣ ተማሪዎች፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ ከሠራተኞች፣ እና ከማህበረሰብ ግብአቶችን ማቀናበር እና፣

    d) ለመጠበቅ/ለማቆየት፣ ለማሻሻል/ለማሳደግ፣ ለማሳደስ፣ ወይም የህንጻውን ሲስተም እና መገልገያዎችን/ፋሲሊቲዎችን ለመተካት ሚዛናዊ የውሳኔ አሰጣጥ።

2. ለአዲስ ትምህርት ቤቶች ቦታ ስለመምረጥ፣ የትምህርት ቤት ወሰን - ክልል ድንበሮችን መቀየር፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች ምስረታ፣ ወይም ስለ ትምህርት ቤቶች መዝጋት ወይም ማጣመር፣ ስለ ትክክለኛነት፣ ሚዛናዊነት የቦርድ ፖሊሲ "Board Policy ACA" እንድምታ እሳቤ በመውሰድ ቦርዱ ስለ ሁሉም ምክረ-ሃሳብ እና የውሳኔ አሰጣጥ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ሚዛናዊነት፣ እና ባህላዊ ብቃት።

3. በየጊዜው፣ ስለፋሲሊቲ እቅድ የማዘጋጀት ሂደት ብዝሃነት በሠፈነበት በሞንተጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች ትርጉም ያለው/አስፈላጊ የትምህርት ጠቀሜታ ለማግኘት የሚችሉበትን እድሎች ይጨምራል።

4. የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ ከባለድርሻ አካላት ግብአት ከተሰበሰበ በኋላ ስለዚህ ፖሊሲ የአፈጻጸም መመሪያ ደንብ ያዘጋጃል።

## I. ግምገማ እና ሪፖርት

1. ስለ ትምህርታዊ ፋሲሊቲዎች የሚዘጋጀው ዝርዝር ዕቅድ ማስተር ፕላን ስለ ፋሲሊቲ ፕላን የማድረግ ሂደት እና የካውንቲው ካውንስል ያፀደቀውና በዓመቱ ውስጥ ቦርዱ ስላከናወናቸው ስራዎች፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተቀበላቸው ተማሪዎች ብዛት እና የተሰጠ አገልግሎት፣ የ MCPS ን ትምህርታዊ ፋሲሊቲዎች በጥሩ ሁኔታ መጠበቅ እና/ወይም ለወደፊት ተግባራዊ የሚሆኑ በካፒታል ፕሮጀክቶች አማካይነት ወይም ሌላ ካፒታል ያልሆነ ስልቶች/ስትራቴጂዎች አቅም ለማጎልበት ትምህርት ቤቶች እና ቦታዎች በዓመታዊ የጁን ወር ህትመት ላይ ይካተታሉ።

2. የሂደቱን ውጤት እና ከፖሊሲው ጋር ይጣጣም እንደሆነ የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ ክትትል ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ እና ለቦርድ ሪፖርት ያደርጋል።

3. ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ክለሳ ይደረጋል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** *Code of Maryland Regulations* §13A.01.05.07 and §13A.02.09.01-.03

***የፖሊሲው ታሪክ፡-*** በውሳኔ ቁጥር 257-86 ስራ ላይ ውሏል፣ ኤፕሪል፣ 28/1986፣ በውሳኔ ቁጥር 271-87፣ ሜይ 12/1987 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 831-93፣ ኖቬምበር 22/1993 ተሻሻሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 679-95፣ አክቶበር 10/1995 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 581-99 ሴፕቴምበር 14/1999 ተሻሽሏል፣ የጽ/ቤት ስያሜዎች ጁን 1/2000፣ ለውጥ ተደርጓል፣ ኖቬምበር 4/2003 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 268-05፣ ሜይ 23/2005 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 282-14፣ ጁን 17/2014 ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር 436-18፣ ሴፕቴምበር 24/2018 ተሻሽሏል።

***ማሳሰቢያ፡-*** Tenets of Board Policy FKB፣የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፋሲሊቲዎች ጥበቃ እና ማዘመን/Sustaining and Modernizing MCPS Facilities በውሣኔ ቁጥር "Resolution No. 436-18" ላይ ተካቷል፣ እና የዚህ ፖሊሲ ማሻሻያ፣ እና ሴፕቴምበር 24/2018 በፀደቀው የቦርድ ፖሊሲ "Board Policy FAA" መሠረት "Policy FKB" ተሠርዟል።